የአማራ ማኅበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ
Federation of Amharas in North America (FANA)

## አገር በአላዋቂዎች ስትመራ አዋቂ ሆኖ መገኘት ወንጀል ይሆናል።

በአብይ አህመድ ቀዳሚነት የሚመራው ኦነጋዊ አገዛዝ ኢትዮጵያን አፈራርሶ በምስራቅ አፍሪካ ከሌሎች ብሔሮች ነፃ የሆነ የኦሮሞ አገር ለመመስረት የሚያደርገውን የቅዠት ጉዞ ለማሳካት በቅድሚያ ከገዛ አገሩ አማራውን ማጥፋት አለብኝ ብሎ በግልጽ እና በስውር የአማራን ዘር ለማጥፋት ኦነጋዊ አገዛዝ መንበረ ሥልጣኑን ለ27 ዓመታት በግፍ ኢትዮጵያን ከገዛው ትህነግ መራሹ ኢህአዴግ ተረክቦ ላለፉት አምስት ዓመታት በተጠና መንገድ አማራን ብቻ እየለየ የፈጸማቸው የጭካኔ ጅምላ ጭፍጨፋዎች ፤ ማፈናቀሎች ፤ አፍኖ መሰወር ፤ የመኖሪያ ቤት ማፍረስ ፤ በሚታወቁ እና በማይታወቁ ማሰቃያ ቦታዎች ማሰር ፤ ያለ ምንም ምክንያት ከሥራ ማባረር እና ሌሎችንም ተዘርዝረው የማያልቁ ግፎች በአማራ ህዝብ ላይ እየፈጸመ እንደሆነ ገሀድ የወጣ ሀቅ ነው።
አረመኔው ኦነጋዊ አገዛዝ በዚህ ሁሉ አማራን የማጥፋት ዘመቻው ሂደት ውስጥ የጥፋት ጉዞውን አስቀድመው የነቁበትን የአማራ ልጆች በማደን እየገደላቸው ከፊሉንም በህግ ስም በየማጎሪያ ቤቱ እያሰቃያቸው እና እንዲሁም አልፎ ተርፎ በኢትዮጵያዊነት እምነታቸው ጠንካራ ሆነው ይህን በአማራ ህዝብ ላይ አገዛዙ እየፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት የሚቃወሙትን እንደ አንጋፋው ጋዜጠኛ እና የታሪክ ጸሐፊ ታዲዮስ ታንቱ አይነቱን በእርጅና ዕድሜያቸው በግፍ በእስር ቤት እያማቀቃቸው እንደሆነም ሁሉም የሚገነዘበው ሀቅ ነው።

አገዛዙ በፍትህ ሥረዓቱ ላይ ከሚፈፅማቸው ቧልት አንዱ የሆነው እ.ኢ.አ ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ሰነድ በተለያየ ዘርፍ ህይወታቸውን የሚመሩ እና ለህዝባቸው ልዩ ልዩ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ 51 የሚሆኑ የአማራ ልጆችን ግማሹን በእስር እያማቀቀ ከፊሉን ደግሞ በሌሉበት "በሽብር" ስም በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕገ-መንግስት እና ሽብር ወንጀል ጉዳዮች ችሎት ክስ እንደቃረበባቸው ለመረዳት ችለናል።

ከነዚህ በአገር ቤት በአገዛዙ ክስ ከተመሰረተባቸው የአማራ ልጆች ውስጥ በተራ ቁጥር 13 ላይ ስሙ የተጠቀሰው እና በሌለበት የወንጀል ክስ የተመሰረተበት አቶ **ጌታቸው በየነ** በአማራ ህዝብ ላይ በመንግስት እየተፈጸመ ያለውን አማራን የማጥፋት ዘመቻ አስቀድመው ከተረዱ የአማራ ልጆች ውስጡ አንዱ ነው። አቶ ጌታቸው በየነ በአማራ ህዝብ ላይ የተደቀነውን አደጋ ከማወቅ በተጨማሪ አደጋውን ለመቀልበስ አማራ በሚኖርበት ቦታ ሁሉ እራሱን ማደራጀት አለበት ብሎ ስለሚያምን እሱ በሚኖርበት በUS አሜሪካ የኮለራዶ ግዛት አማራውን ከማደራጀቱ በተጨማሪ በሌሎች የአሜሪካ ግዛቶች የአማራ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ ብቻ ሳይሆን እነዚህ ማኅበራት በተሻለ ኃይል ለአማራው ወገናቸው በተለያየ መልክ ድጋፍ ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በምክትል ፕሬዝዳንትነት የሚመራውን የሰሜን አሜሪካ የአማራ

ማኅበራት ኅብረት(FANA) ለመመስረት ብሎም በሌሎች ክፍለ አህጉር የተመሰረቱ የአማራ ማኅበራትን በማስተባበር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰረተውን እና አቶ ጌታቸው በህዝብ ግንኙነት በሃላፊነት የሚመራውን ዓለም አቀፍ የአማራ ንቅናቄ(iAM) እንዲመሰረት ክፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ቀደም ሲል ከተለያዩ የኦሮሞ ክልል እና ከቤኒሻንጉል ክልል አካባቢዎች በግፍ የተፈናቀሉትን ፣ በአጣየ እና አካባቢዋ በኦነግ ኃይሎች በተፈጸመባቸው ጥቃት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን ፣ በአማራ እና አፋር ህዝብ ላይ በትግራይ ወራሪ ኃይል የተፈጸመውን ወረራ ተከትሎ በሰሜን ጎንደር ፣ ሰሜን ወሎ ፣ ደቡብ ወሎ ፣ አፋር ዱብቲ ሆስፒታል ጉዳት የደረሰባቸውን ለመርዳት በተቋቋመው Amhara Emergency Fund(AEF) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ ከማገልገል በተጨማሪ AEF በተለያየ ጊዜ ከህዝብ ያሰባሰበውን እርዳታ ለህዝብ ለማድረስ የተጓዘውን የልኡካን ቡድን በመምራት ከሁለት ጊዜ በላይ ቤተሰቡን ትቶ ከሚኖርበት አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ በመጓዝ ለወገኖቹ በፍጹም ተቆርቋሪነት የለፋ እንጂ ኦነጋዊው መንግስት እንደሚለው ወንጀለኛ አይደለም።

አቶ ጌታቸው በየነ በሚዲያው ረገድ በክፍተኛ ደረጃ የአብይ አገዛዝ አማራን የማጥፋት ሴራውን በማጋለጥ ከባልደረቦቹ ጋር በመሆን **በማገር ሚዲያ** ላይ የሚሰራቸው አማራን የማንቃት ስራ ለኦነጋዊ መንግስት ከተነሳበት አማራን የማጥፋት አላማ አንፃር ወንጀል መስሎ ሊታየው ቢችል እና በወንጀለኝነት ክስ ቢመሰርትበት የሚገርም አይሆንም። አብይ ለሚመራው ኦነጋዊ አገዛዝ እያንዳንዱ አማራ ወንጀለኛ እና እንዲጠፋ የተበየነበት ለመሆኑ በትእዛዝ ሳይሆን በራሳቸው ነፃ ህሊና ዳኝነት በህግ ፊት ነፃ ብለው አንዳንድ ዳኞች ያሰናበቷቸው ወንድሞቻችንን ባሰማራቸው ገዳይ ኃይሎች እያሳደደ እንደሆነ ይታወቃል።

ስለዚህ በዚህ ቧልት አይሉት ወይም ቁምነገር የወንጀል ክስ እና እስር እየተንገላታችሁ ያላችሁም ይሁን አቶ **ጌታቸው በየነን** ጨምሮ በሌላችሁበት ክስ የተመሰረተባችሁ የአማራ ልጆች ይህ ኋላ ቀር እና አረመኔ ኦነጋዊ ስብስብ ተወግዶ የአማራው ህልውና ከማንኛውም ኃይል ከሚመጣ ስጋት ነፃ ሆኖ በአገሩ በሰላም እና እኩልነት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በነፃነት መኖር እስኪችል ድረስ የጀመራችሁትን ለህዝባችሁ ድምፅ የመሆን እና የማንቃት ሥራ ለአፍታም ቢሆን ቸል እንዳትሉ የአማራ ማኅበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ(FANA) እያሳሰበ ኅብረቱ በሚችለው ሁሉ ከጎናችሁ እንደሚቆም ቃል ይገባል። በተጨማሪም በአገር ቤትም ይሁን ከኢትዮጵያ ውጭ የምትኖሩ የአማራ ልጆች ሁሉ ከምንጊዜውም በበለጠ አገዛዙ በአማራው ላይ የከፈተውን ሁሉን አቀፍ ጦርነት ለመቀልበስ በሚደረገው እራስን የመከላከል ትግል ማንንም ሳትጠብቁ በግለሰብ ደረጃም ይሁን በያካባቢያችሁ ያሉ ድርጅቶችን በመቀላቀል ታሳሪዎችን እና ቤተሰቦቻቸውን ከመጠየቅ ጀምሮ ሌሎች ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማበርከት የየበኩላችሁን አስተዋፅኦ የምታደርጉበት ጊዜው አሁን እንደሆነ አበክረን እያሳሰብን የሰሜን አሜሪካ አማራ ማኅበራት ኅብረት አባላት የሆን ሁሉ ከቁርጠኛው መሪያችን ከአቶ ጌታቸው በየነ ጎን በጽናት መቆማችንን እናረጋግጣለን።

ህልውናችን በትግላችን!
ክንዳችን መዳኛችን!

FANA